# *ቀዳሚተ ሰንበትን ከጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ጋር*

## *በሲያትል*

ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደን በዝና አውቀነው ቆይተን ነበር። ወደዝህች ምድር በነጻ ፈቃዳችን እንኖር ዘንድ የላከን እግዜር ፈቅዶ ይሄው በአሲምባ ሬስቶራንት ተገናኘን። አሲምባ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ የአንድ ትልቅ ተራራ ስም ነው። በዚህ ተራራ ሥር አገራቸውን ነጻ ለማውጣት ሲሉ የቀደሙ ወንድሞችና እህቶች የመሸጉበት ታሪካዊ ሥፍራ እንደሆነ ስምተናል። ይህ ታሪካዊ አምባ ተረስቶ አልቀረም ይሄው በፈረጀቹ አገር የአንድ ግሩም ሬስቶራንት መጠሪያ ሁኗል። በዚህ ሬስቶራንት ውስጥ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደን አግኝተን ብዙ ጥያቄ ጠየቀነው። ከእርሱም ጋር በላን ጠጣን። ደስም አለን።

ዳዊት ከበደ መለስ ዜናዊ ተውልዶ ካደገበት አድዋ ከተማ ነው የተወለደው። አድዋ እንደ መለስ ዜናዊ የመሰለውን ክፉ ሰው ብቻ ሳይሆን ዳዊት ከበደን የመሰለ ምርጥ ኢትዮጵያዊያንንም ትወልዳለች።ዳዊት ከበደ በመለስ ዜናዊ አማካኝነት በተዘጋጀ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሶ ለሁለት ዓመት ያህል በቃሊቲ ታስሯል። በመለስ ዜናዊ አባባል ዳዊት ያጠፋ የነበረው የትግራይ ዘር ነው። ይህን አሳፋሪ ክስ ስንሰማ መለስ ዜናዊን ንቀን እናልፈዋለን እንጂ ሌላ የምንለው ተጨማሪ ነገር የለንም። ዳዊት ከበደ ግን በወጣትነቱ ኢትዮጵያዊያን አማራጭ መረጃ ማግኘት አለባቸው ብሎ በጽናት የቆመ ጀግና ነው። ጀግና ማለት እንደነመለስ ዜናዊ ህጻን ልጅን ግንባሩን በጥይት በርቅሶ ሜዳ ላይ መጣል ሳይሆን እንዲህ ለእውነት ጸንቶ መቆም ነው። ጀግንነት ማለት በሚያስፈራ ድባብ ውስጥ ሁኖ ትክክለኛ የሆነን ነገር ማድረግ መቻል ነው። ከዚህ አንጻር ዳዊት ጀግና ነው።

ዳዊት ከበደ እንደ ኢትዮጵያ ገዥዎች አባባል ከሆነ "ይቅርታ ጠይቆ" ከእስር ተፈቷል። ዳዊትም ለዚህ ጥያቄ ተጠይቆ የሰጠው መልስ "አዎን ይቅርታ ጠይቄ ነው የተለቀኩት" ብሏል።የኢትዮጵያ ገዥዎች በይቅርታ ከለቀቁት በኋላ ግን አንበርክከን አስለምነን ከእስር ለቀቅነው ብሎ ያለምንም እፍረት በትልቅ ኩራትና ድንፋታ በመገናኛ ብዙሃን ሲያወሩ ከርመዋል።ይህን የሰማን ኢትዮጵያዊያን አባቶቻችን ያስተማሩን ወግና ባህል በኢትዮጵያ ገዥዎች እንዲህ አፈር ከድሜ ሲበላ በእጅጉ አዝነናል።እነ አቶ መለስና በዙሪያቸው የተኮለኮሉ ኮበሌዎች ኢትዮጵያዊ የሚያሰኙንን መልካም ወግና ልማዶቻችንን እንዲህ እያዋረዱ ኢትዮጵያን የማፈርስ ተግባሮቻቸውን በትጋት እያከናወኑት ነው።እኛ እንደተማርነውና እንደምናውቀው አንድ ግዜ ይቅር ከተባለ ይቅር ነው። በቃ አለቀ።ተንበርክኮ አልቅሶ ለምኖኝ እየተባለ ማውራት እጅግ ነውር ነው።ከባህልም ውጭ ነው።ያ ሁሉ የገዥዎቻችን ድንፋታ ባህልን ካለማወቅ የተነሳ ሳይሆን ሆን ተብሎ ኢትዮጵያዊ ወግና ባህልን ከማራከስ ፍላጎት የመነጨ የእኩይ ፍላጎታቸው መገለጫ እንጂ።

ዳዊት ከበደ በይቅርታ ቢፈታም ነጻ አይደለም።ነጻ አለመሆኑን ደግሞ ከንግግሮቹና ከሚሰጠው መልስ ለመረዳት ችለናል።በነጻነት እንኖር ዘንድ ተፈጥረን ስናበቃ ጨካኞች በራሳችን ላይ ነግሰውብን ይሄው የጻፊዎቻችንን ነጻነት ነፍገው የስቃይ ህይወት እንዲኖሩ አድረገዋቸዋል።በካንሰር በሽታ የሚሰቃይ ሰውና በነጻ ሂሊና የማይጽፍ ጋዜጠኛ የስቃያቸው መጠን እኩል ነው።ዳዊት በይቅርታ ከቃሊት ከተለቀቀ በኃላ ሌሎች ስድስት አዳዲስ ክሶች አሉበት።እነዚህ ክሶች በተፈለጉ ግዜ ተመዘው ይህ ወጣት ጋዜጠኛ ቃሊት ላለመግባቱ ምንም ዋስትና የለውም።በዚያች አገር ውስጥ የዳዊትን መብት የሚጠብቅለት ህግ በሌለበት ምድር ነጻ ነው ብለን ለማመን እንቸገራለን።ይህ ነገር የከነከናት አንዲት እህት ዳዊት እዚህ አሜሪካን እንዲቀር ጠይቃው ነበር።ዳዊት ግን ህዝቤን ለማን ትቼ ብሎ ሲያበቃ የሚቀጥለውን ቅኔ ከጥላሁን ገሰሰ ዜማዎች መዝዞ ለሀገሩ ለኢትዮጵያ ተቀኝቶላታል፡

*በእናት አገር ምድር ከሚያውቀኝ ከማውቀው፤*
*ስቃይ መከራየን ካንቺ ዘንድ ያድረግው።*
*ፍቅርሽ ላኖረኝ ሰው ላረግኝ ፍቅርሽ፤*
*እድሜየን ያድርገው ውለታሽን መላሽ፤*
*ለጥቃትሽ ጋሻ ለችግርሽ ደራሽ።*

መቸስ ያገር ልጅ ሲሰበሰብ ጨዋታው ማማሩ።ብዙ ሳቅን ብዙ ተጫወትን።ብዙም ጥያቄዎችን ጠየቅን።አንዳንዶቹ ጥያቄዎችማ ጋዜጠኛውን መልሶ እስር ቤት የሚከቱት ነበሩ።ጋዘጤኛው ግን በብርቱ ጥንቃቄ መልሷቸዋል።በጥንቃቄ ስል

ከልብ በጥናቃቄ ማለቴ ነው።ውጭ አገር ሂዶ እንደልብ ተናግሮ የት ሊገባ? ያው እዚያ ቃሊት ካልሆነ።እኛም ሆንን ጋዜጠኛው ዳዊት ብርቱኳን የደረሰባትን አሳር እናውቃለን።ስለዚህ ወደ አገር ቤት የሚመልሱ ሰዎች በነጻው ምድር ሁነው በነጻነት እንዳይናገሩ የታወቀ እገዳ አለባቸው።ነጻነት ሰጥቶ የፈጠረን እግዚአብሄር ነጻነታችን ባልባሌ ሰዎች ሲወሰድ ባለመከላከላችን አዝኖብናል።እግዚአብሄር የሰጠንን በረከት አስወስደን ያለበረከት የቀረን ሚስኪን ዜጎች ሁነናል።ነጻነት በረከት ነው።በረከት የሌለው ህዝብ ደግሞ ሁልግዜም ርሃብተኛ ነው።እኛን የተራብነው ምግብ ብቻ ሳይሆን ነጻነታችንም ጭምር መሆኑን ተገንዝበን የተነጠቅነውን በረከታችንን ለማስመለስ የምር ትግል ያስፈልገናል።ትግል የሚለውን ቃን ያማትወዱ ካላችሁ ደግሞ ወደ እግዚአብሄር መጮህ ይጠበቅባችኋል።ከልብ የሆነ ጩኸት አምባገነኖችን ይቅርና የኢያሪኮን ግንብ አፍርሷል። ያለነጻነት መኖር ጽድቅን የሚያስገኝ ደግ ነገር አይደለም።ያ እግዜርን የሚያመልክ ሰውም ተግባር አይደለም።

በነጻ ዓለም እየኖርን ነጻ ያልሆንን ያልታደልን ዜጎች ነን እያልን ማማረራችንን ትተን በያለንበት ለነጻነት የሚከፈለውን መስዋእትነት ለመክፈል እንነሳ። ምክሬ ደግሞ ይህች ነች፡

*"ጎበዝ ዝም አትበሉ ዝምታ ለበግም አልበጃት፤*
*አሥራ ሁለት ሆና አንድ ቀበሮ ፈጃት።"*

ጋዜጠኛ ዳዊት የከፈለውን መስዋእትነት ምክንያት በማድረግ ምስጋና ሊያቀርቡለት ብዙ ኢትዮጵያዊያን ተገኝተው ነበር።ምሁራን የህግ ባለሙያዎች ጋዜጠኞች የፖለቲካ ድርጅት አባላት የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች እና ሌሎችም ተገኝተዋል።ፍጹም ሰላም የሞላበትና ገንቢ ውይይት የተደረገበት ብቻ ሳይሆን ጥሩ የሆነ ወንድማማችነት የሰፈነበትም ምሽት ነበር።በዚህ ፕሮግራም ላይ ወያኔ/ኢህአዴግን እወክላለው የሚል ኮበሌ ባለመገኘቱ ዘራችን ኢትዮጵያዊነት ሁኖ አመሸ።እኛም የአንዲት አገር ልጆች በአንድ ቋንቋ የልባችንን ስንጨዋወት አምሽተናል።እስይ እንኳንም ኢህአዴጎች ከእኛ ጋር ያልኖሩ።እነርሱ ያሉበት ሳቅ የለም።አዎን እነርሱ እኛ ዘንድ ባለመኖራቸው ሳቅ በሳቅ ጨዋታ በጨዋታ ሁነናል።ግሩም ምሽት።

መቸስ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁኖ በአገራችን መሪዎች ላይ መቀለድ በስም ማጥፋት ወንጀል አስይዞ ዘብጥያ የሚያሰወርድ ነው።ኢህአዴግ/ወያኔ እዚህ ስለሌለ ነጻነታችን የተጠበቀ ነው።የጋዜጠኛ ዳዊት ከበደን ነጻ መሆን ግን እንጠራጠራለን።እርሱ ያዳምጣል ይስቃል እንጂ አዲስ አበባ ያሉት መሪዎች ላይ ሲቀልድ አልሰማነውም።ዳዊትን ለማክበር የመጡ ወንድምና እህቶች ካካፈሉን ቀልድ እና እኛም የሳቅንበትን እናንተም ፈገግ ትሉ ዘንድ ለወዳጆቻችን ማካፋልን ወደናልና።እነሆ በረከት፤

እስኪ ለመሆኑ የኢትዮጵያዊ ፕሪዝዳንት ሙቶ አለቃ ግርማ እድሜያቸው ስንት ዘመን ይሆን ? እርሳቸው ወደውና ፈቅደው የመሳቂያችን ርእስ ሁነው አመሹ።ሙቶ አለቃ ሲባሉ አይወዱም አሉ ሆኖም ግን እርሳቸው ሙቶ አለቃ ናቸው እንጂ ሌላ ምንም አይደሉም።የእድር ዳኛ እንደነበሩ በሹመታቸው ወቅት በመለስ ዜናዊ ሲነገር ስምተናል።ይህ ደግሞ መጠሪያ ሊሆን አይችልምና በሙቶ አለቃነታቸው ጸንተናል።

አንድ ቀን ሙቶ አለቃ ግርማ አንድ ዝግጅት ላይ ጥሪ ተደርጎላቸው ሄዱ አሉ።እዚያ ዝግጅት ላይ ከሰው ሁሉ ፊት ቁጭ ብለው አንደ አንበሳ እያጓሩ ይተነፍሳሉ። አንድ ተንኮለኛ የፕሮቶኮሉን ኃላፊ ጠርቶ ምን ሆነው ነው እንዲህ የሚተነፍሱት ብሎ ይጠይቃል። አይ ጌታየ ክቡር ፕርዝዳንቱ አየር የሚስቡት ከግልገል ግቤ ሁለት ነው ብሎ እርፍ። መቸስ እንደሚያስቃችሁ እንገምታለን።ራሳቸው ሙቶ አለቃ ግርማም ቢሆኑ ፈገግ ማለታቸው አይቀርም።

አቶ መለስ ነፍሳቸው አይማርም። ያለቀላቸውን ሽማግሌ ሰው ፕሬዝዳንት አድርጎ በእግዜርን ፍጡር እንዲህ መሳለቂያ አድርገው እንዴት ነው መንግስተ ሰማያት የሚገቡት? ለመሆኑ ሙቶ አለቃውስ ለምንድ ነው በቃኝ የማይሉት ?ሙቶ አለቃ እስኪ ምክር ይሰሙ እንደሆነ ልምከርዎ "በቃኝ ማለትን ተማሩ" ብሎ ሃዋርያው ቅዱስ ጵውሎስ የጻፈው ለእርሶ ነው።እባክዎትን በቃኝ በሉና አርፈው እቤቶት ይቀመጡ።

የሙቶ አለቃ ግርማ ነገር እንደ አለቃ ገ/ሃና ተወርቶ የሚያልቅ አይደለም። ሌላ ቀን ደግሞ እንዲህ የሚል ሃሜት ታምተዋል አሉ። እንዳው ዶ/ር ነጋሶን የመሰለ ፕሬዝዳንት አውርዳችሁ ይህኙን ሽማግሌ ለምንድ ነው የምታደክሙት

ብለው ጠያቂዎች ይጠይቃሉ። አንዳንድ ክፉ መልስ ሰጪዎች ደግሞ መቸስ መልስ አያጡም። አፋቸውን ሞልተው ወያኔ ከስህተቱ የሚማር ድርጅት ነው። ነጋሶ እንዴት ስብሰባ ረግጦ እንደወጣ አይታችኋል። ከዚህ ኢህአዴግ ጥሩ ትምህርት አግኝቷል። “ለዚህ ነው በራሱ ብድግ ብሎ ስብሰባ ረግጦ የሚወጣ ፕሬዚዳንት ያልተፈለገው” አሉ ይባላል።

መቶ አለቃ በወጣትነታቸው አራዳ ነኝ ከሚሉ ጎርመሶች መካከል የሚመደቡ ነበሩ።የወጣትነታቸውን ዘመን የሚያስታውሱት በዳንስ ነው። ሰው እጅ ጠባብ በሚለብስበት በዚያ ዘመን እርሳቸው ጅንስ ታጥቀው ይውረገረጉ ነበር አሉ። አሁን ታዲያ አንገታችውን ቀና አድርገው በኩራት የሚናገሯት አንዲት ገድል አለቻቸው።አንዱ ኤርትራዊ እነ መለስ ዜናዊ ቢያባርሩት እዚያ ወዲያ አስመራ ደርሶ የኢትዮጵያን ህዝብ ሹካና ማንኪያ መያዝ ያስተማርኩት እኔ ነኝ ብሎ መደንፋቱን ሰምተነው ነበር።ይህ የኢትዮጵያ ህዝብ የማይደነፋበት የለም ብለን ነገሩን ሰምተን እንዳልሰማን ሆነን  ዝም ብለናል። እንዲዚሁም ሁሉ መቶ አለቃ  ግርማ በኩራት ፈገግ ብለው ‘እኔ ግርማ እኮ ነኝ ለመጀመሪያ ግዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ዳንስ የጀመርኩት’ እያሉ ይናገራሉ አሉ።መቶ አለቃ ግርማ ዳንስ ስላስተማሩን እናመስገናለን እንበልዎ እንዴ ?

ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደን ብለን ያበሻ ልጆች ተሰባስበን ስንስቅ ስንደሰት አመሸን።ይህ የደስታችን መነሻ የሆነው ጋዜጠኛ አስከ አሁን ስድስት ዓይነት ክሶች አሉበት።እርሱን የማሰርና የመፍታት መብቱ ያሏቸው እነዚያ የዘመኑ ገዢዎቻችን በፈለጉ ግዜ ዘብጥያ ሊያወርዱት እንደሚችሉ ነፍሳችን ነግራናለች።ለምን እስከ አሁን ዝም አሉህ ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ “ህይን ጥያቄ ከሳሾቼ ቢመልሱት ይሻላል”ሲል ባጭሩ መልሶታል።ስድስት ክስ ቢኖርበትም ዳዊት ወደ አገሩ ይመለሳል።እኛም እንደ ዳዊት ከበደ ያሉ ጋዜጠኞች በርትተው እንዲጽፍ አገራችን ኢትዮጵያ ከዘመኑ ዘረኞችና ጨቋኞች እጅ እስከምትላቀቅ ድረስ ጸንተን እንታገል።መታገል የማንፈልግ ደግሞ በጸሎት እናግዛቸው።ስድስት ክስ ያለበት ባንዱ አንድ ቀን ተይዞ መታሰሩ አይቀርም።ያሳሪዎችን ዓይንና ጆሮ እንዲይዝልን በርቱና ጸልዩ።እኛም የምንችለውን እናደርጋለን።

ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደም በዚህ ሁሉ አፈና ውስጥ ሁነህ ስለጻፍክ ጀግና ተብለህ ተሸልመሃልና እንኳን ደስ አለህ እላለሁ።እንኳን ደስ አለህ ስልህ ግን ያለ ነጻነት መኖርህ አንጀቴን እየበላኝ መሆኑን ሳልገልጽልህ ማለፍ ልቤ አልፈቀደምና ይህችኑ ሃዜኔን እወቅልኝ።

ዳዊት ከበደ ገና ወጣት ነው።ገና ብዙ እንደሚሰራ እንጠብቃለን።እርሱ ብቻ ሳይሆን አውራባ ታይምስ ላይ የሚሰሩ ወጣቶች በሙሉ ያች አገር ነጻ አስከምትወጣ የሚከፍሉት መስዋእትነት ቀላል አይሆንም።

አይዟችሁ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እኛም አለን ከጎናችሁ።ለነጻነታችን የምንችለውን ብቻ ሳይሆን ከዚያ በላይ እንድንሄድ የሚያስገድደን ሁኔታ ውስጥ እንደሆንን በደንብ ተገንዝበናል።አዎን አገራችን ነጻ ትወጣለች።እነዳዊትም ሂሊናቸው የፈቀደላቸውን ብቻ  በነጻነት ይጽፋሉ።ያን ግዜ ጋዜጠኞቻችንን የሚያስፈራሩ ጨካኝ ገዢዎች አይኖሩም። የእፎይታ ዘመን በፍጥነት ይመጣል።

አሁንም በድጋሚ ወንድማችን ጋዜጠኛው ዳዊት ከበደ እናመሰግንሃለን።

ሰላም እንሁን።

ስሜ ዳዊት ነው።